# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከማርች 1-10 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከማርች 11-20 እና ከማርች 21-30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## 1. እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምዕራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግበዋል፡፡ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በሐሮማያ 6.5፣ በአልጌ 6.5፣ በአማን 5.2፣ 14.2፣ 8.6፣ በአምቦ 14.5፣ በአንገርጉትን 6.6፣ በአርባምንጭ 26.5፣ በአርጆ 16.4፣ 26.2፣ 16.6፣ 8.4፣ በአዋሽ አርባ 11፣ በሀዋሳ 6፣ 29.5፣ በባቱ 10፣ በበደሌ 5.8፣ በብላቴ 13.8፣ በቦሬ 8.5፣14.2፣ በቡርጂ 10.7፣ 57.2፣ በጭራ 13.5፣ 17.5፣ በኮምቦልቻ 27.7፣ በደብረማርቆስ 7.2፣ በዲላ 5.7፣11፣ በድሬደዋ 8.2፣7.2፣ በኢጃጂ 7.7፣ 9.7፣ በእነዋሪ 7.6፣ 6፣ በፍቼ 9.5፣ 24.8፣ በጋቲራ 14.8፣ 22.6፣ 28፣12.2፣ በገለምሶ 7.6፣ በወሊሶ 7.2፣ 8.9፣ በጉንዶ መስቀል 13፣ 6.7፣ በቡሌ ሆራ 27.4፣ 13.7፣ በሆሳዕና 14፣ 38.6፣ 38.3፣ በነገሌ 17.2፣ በነቀምት 12፣ በእምድብር 5.1፣ 5.1፣ 17.1፣ 6.4፣ በጅማ 10.6፣ 14.5፣ 12.2፣ በጅንካ 18፣ 7.2፣ 19.7፣ በካቺሴ 8.3፣ በኮንሶ 25፣ 6.5፣ በቁሉምሳ 8.8፣ በላሊበላ 5.8፣ በሊሙገነት 5.3፣ 6.3፣ 16.7፣ 13.8፣ በማጂ 10.7፣ 8.7፣ 10.8፣ በማሻ 20፣12፣ በመህልሜዳ 6፣ በመካነሰላም 6.6፣ በምዕራብ አባያ 15፣ በሞያሌ 12፣ 5.6፣ በንፋስ መዉጫ 6.3፣ 6.0፣ በኑራ ኤራ 16.2፣ በሳዉላ 50፣ 9.5፣ በሰኮሩ 6.6፣ 15.5፣ 22.5፣ በቴፒ 5.7፣ በተርጫ 5.8፣ 30.6፣ 16.2፣ 7፣ ጽጽቃ 6.0፣ በወገል ጤና 8.1፣ በወራቤ 21.4፣ 7.4፣ በወረኢሉ 10.6፣ 14.7፣ 6.6፣ በወላይታ ሶዶ 7.0፣ 8.6፣ እንዲሁም በያቤሎ 5.1 ሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ እና በሰሜን ምዕራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከ10 -100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣የሰሜን የምዕራብ እና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ የሸበሌ እና የቆራሄ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ጋምቤላ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35.0-43.5 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4)፡፡




የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከረጅም
ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር

ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ወር የመጀመሪያው አስር ቀናት አጋማሽ በኋላ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበር ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች አመልክተዋል። ይህም የተገኘው እርጥበት በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖራቸው ያስቻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የማሳ ዝግጅት ለማድረግ እና የተለያዩ ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚበቅሉ ቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የመካከለኛው እና ታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው ምስራቃዊ እና መካከለኛው ኪስ አባይ፣ በጥቂት በላይኛው እና ታችኛው አዋሽ እና ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም ታችኛው ኦጋዴን እና በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተለይም በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ እና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም የውሃ ፍስት በመጠኑም ቢሆን ከመጨመር አንጻር አዎንታዊ ጎን እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ አባይ ፣አይሻ፣ መረብ ጋሽ እና የታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ወር ነው፡፡ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል፡፡ በማርች የሚኖረው የዝናቡ መጠን ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ እስከ 30% የሚያገኙ ሲሆን፤ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ከ20%-40% የሚሆነዉን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ፡፡ በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የወቅቱ ዝናብ አብዛኛውን የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚሸፍን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ ስለሆነም የሚኖረው የዝናብ መጠንና ስርጭት የበልግ የግብርና ስራዎችን ለማከናወን ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 7) ፡፡

### 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚያገኙ ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ቀላል መጠን ያለው ዝናብ የሚያገኙ ቦታዎች




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ | መካከለኛ መጠን |
| | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን |
| | ኮንሶ፣ አሌ፣ እና ደቡብ ኦሞ | ቀላል መጠን |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን፣ ኤረር፣ ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች | ቀላል መጠን |
| አማራ | የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ሰሜን ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| ትግራይ | የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ሀላባ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ ኑኤር፣ መዠንግ እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን |
| አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በማርች ወር በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በማርች የሁለተኛዉ አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ40 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)።



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄደው ከማርች አጋማሽ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በማርች ሶስተኛው አሥር ቀናት አብዛኛዎቹን የበልግ አብቃይና ተጠቃሚ ቦታዎችን ያካተተ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይስተዋልባቸዋል፡፡ በመጪዎቹ የማርች ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማለ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.5 እ.አ.አ ከማርች 11-20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው አስር ቀናት በደቡብ፤ በመካከለኛ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀውና በርካታ ቦታዎችን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የአፈር ውስጥ የውኃ መጠንን ስለሚያሻሻል በማርች ወር ለሚዘሩ ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማከናውን፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል። በአንፃሩም በተለያዩ ምክንያቶች ዘር ለመዝራት የዘገዩ አካባቢዎች የሚጠበቀውን እርጥበት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና በቂ ዘር ለመዘራት የሚያሰቸል ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ አርሶ አደሮች፣ አርበብቶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት ከታች በተቀመጠው የግብርና ምክረ ሀሳብ መሰረት የቅድም ጥንቃቄ ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት ስምንት ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ዋግ ህምራ፣ ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች ዳውሮ፣ ከፋ ሸካ እና ኮንታ | መጠነኛ እርጥበት | • ለማሳ ዝግጅት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል | • ዘር ለመዝራት በቂ ያልሆን የአፈር እርጥበት<br>• የመኖ ሰብሎችን ለመዝራት የእርጥበት እጥረት<br>• ከፍተኛ ትነትና ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት | • የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የዲጋፌ መስኖ የዝናብ ውሃ ማሰባባሰብ<br>• በሰብል ማሳ የውሃ መከተር ማከናወን<br>• ተለዋጭ የእንስሳት መኖ ማከማቸት<br>የሚገኘውን ውሃ በቁጠባ እና በጥንቃቄ መጠቀም |
| ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ዞኖች | እርጥበታማ | • የማሳ ዝግጅት ለማድረግ<br>• ዘር ለመዝራት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት | • የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የዲጋፌ መስኖ የዝናብ ውሃ ማሰባባሰብ<br>በሰብል ማሳ የውሃ መከተር ማከናወን |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.6 እ .ኤ. አ ከማርች 11-20 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ የተሻለ እርጥበት ያገኛሉ።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በተፋሰሶች ላይ

| ተፋሰስ ና ንዑስ ተፋሰሶች | የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| ኦሞ ጊቤ (የላይኛውና መካከለኛው ንዑስ ተፋሰሶች) | መካከለኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል | • በታችኛው ንዑስ ተፋሰስ ደረቅ ሁኔታ<br>• ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት | • ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል<br>• የዝናብ ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብና ማጠራቀም |
| አባይ ተፋሰስ( የላይኛው ምስራቃዊ ንዑስ ተፋሰሶች) | መጠነኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የግድቦች ውኃ መጠነኛ ማሻሻል | • ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት<br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን |
| ኦሞ ጊቤ( የላይኛው እና መካከለኛ ንዑስ ተፋሰሶች) | | | | |
| አዋሽ፣(በላይኛውእና መካከለኛ ንዑስ ተፋሰሶች) | | | | |
| በስምጥ ሸለቆ፣(በላይኛው ንዑስ ተፋሰሶች) | | | | |
| ባሮ አኮ(የላይኛው) | | | | |
| የላይኛው ዋቢ ሸበሌ | | | | |



ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዋቢ ሸበሌ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ አይሻ እና መረብ ጋሽ (በሁሉም ንዑስ ተፋሰሶች) | ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ | | ከፍተኛ ትነት<br>• የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ<br>• ንጹህ የመጠጥ ውኃ አርቦት እጥረት<br>• የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ | • ትንበያዎችን በቅርበት በመከታተል የውኃ አስተዳደርን መምራት<br>• በተለያዩ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር<br>• የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |



ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et